
# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በኖቬምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት በአብዛኞዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሐያማ፣ ነፋሻማና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል። በተጨማሪም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡና ደቡብ ምሥራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከዕለት ወደ ዕለት እየቀነሰ መምጣቱን መረጃዎች ያመለክታሉ። ይሁን እንጂ ከነበራቸው የደመና ሽፋን አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በአንዳንድ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች እንዲሁም በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ ኪስ ቦታዎች ላይ ዝናብ ነበር። በሌላ በኩል ከደመና ሽፋን መቀነስ ጋር ተያይዞ የማለዳውና የሌሊቱ ቅዝቃዜ ተጠናክሮ የነበረ በመሆኑ፤ በሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለመጥቀስ ያህል በደብረ ብርሃን -1.6፣ በመሀል ሜዳ -1.2፣ በሀሮማያ 0.0፣ በወገል ጤና 0.5፣ በአምባ ማርያም 1.0፣ በአርሲ ሮቤ 1.0፣ በባቲ 1.6፣ በአዲግራት 2.0፣ በደብረዝት 2.0፣ አዲስ አበባ ቦሌ ኢንጂነሪንግ 2.0፣ በቡኢ 2.0፣ በአደሌ 2.2፣ በሾላ ገበያ 2.5፣ በእነዋሪ 2.5፣ በአይደር 3.0፣ በወንበራ 3.0፣ በማይጨው 3.2፣ በፍቼ 3.3፣ በሮቤ 3.5፣ በጨፋ 3.8፣ በእንድብር 3.8፣ በኮፈሌ 3.8፣ በአፀቢ 4.0፣ በቦሬ 4.2፣ በጃራ 4.2፣ በወረኢሉ 4.5፣ በደባርቅ 4.5፣ እንዲሁም በጅማ 5.0 በዲግሪ ሴልሽየስ መመዝገቡ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማውቅ ተችሏል።


ባለፉት አሥር ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-60 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ የአሶሳ ዞን፤ ጥቂት የሰሜን ጎንደር ደቡባዊው ክፍል፤ ከጋምቤላ ዞን 1ና 2፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የቤንች ማጂና የደቡብ ኦሞ፤ ከኦሮሚያ ምዕራብ ወለጋ፣ የቦረና እንዲሁም የአርሲና የባሌ ዞኖች፤ ከሶማሌ የጎዴ፣ የደገሀቡር፣ የአፍዲርና የሊበን ዞኖች ከ2-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው። የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 1 እና 2)።

በአሥሩ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ የአሶሳ ዞን፤ ጥቂት የሰሜን ጎንደር ደቡባዊው ክፍል፤ ከኦሮሚያ ምዕራብ ወለጋ፣ የቦረና እንዲሁም የአርሲና የባሌ ዞኖች፤ ከሶማሌ የጎዴ፣ የአፍዲርና የሊበን ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ቆይተዋል (ካርታ 3)።


ካርታ1   ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2   እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



**ካርታ3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር**




## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11- 20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ሁለተኛዉ የኖቨምበር አስር ቀናት በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማዉ እርጥበት ከፀሃያማነትና ከነፋሻማነት ጋር እንዲሁም ከማለዳና ከሌሊቱ ቅዝቃዜ ጋር ተዳምሮ በአመዛኙ ተስተዉሏል፡፡ ከሚጠበቀዉ ወቅታዊ የግብርና እንቅስቃሴ አንጻር የተስተዋለዉ ፀሃያማና ነፋሻማ ሁኔታ የደረሱ ሰብሎች በጊዜ እንዲደርቁ ከፍተኛ ሚና የነበረዉ ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ ሰብል ለመሰብሰብና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን ምቹ እንደነበረ ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል በደቡብና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የታየዉ የእርጥበት መቀነስ በተለይም የበጋን ወቅት እንደ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ለሚጥቀሙ የአርብቶ አደርና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚያከናዉኑት ተግባር አሉታዊ ሚና እንደነበረዉ ይገመታል፡፡ በአንጻሩ ከደረቃማዉ የአየር ሁኔታና ከደመና ሽፋን መሳሳት ጋር ተዳምሮ በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፈሎች ላይ የማለዳውና የሌሊቱ ቅዝቃዜ ተጠናክሮ እንደነበረ መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፤ በተለይም በአንዳንድ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በይበልጥ የተጥናከረበትና በአንደንድ አካባቢዎች ላይም ከ 5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች የሆነ ዝቅተኛ ሙቀት ተመዝግባል፡፡ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ባልደረሱና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች እድገት ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 11-20 ኖቨምበር 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ ጥቂት የመካከለኛውና የሰሜን ምእራብ ደቡባዊው ክፍል በሆኑ የአገሪቱ ተፋሰስ ኪስ ቦታዎች ላይ ከፍተኛ እርጥበት እንዲሁም ጥቂት የመካከለኛው እና የአባይ ደቡብዊው ክፍል ተፋሰስ ኪስ ቦታዎች ላይ መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በደቡብ፣ በመካከለኛውና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ተፋሰስ ኪስ ቦታዎች እርጥበታማ ሁኔታ የተስተዋለባቸው ናቸው፡፡ ይህንን ተከትሎ የአባይ ደቡባዊ ክፍል፣ የላይኛው ስምጥሸለቆ እና አዋሽ ኪስ ተፋሰሶች ከከፍተኛ እሰከ መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ የተቀሩት አብዛኛው የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## **<u>እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30/2017 የሚኖረው</u>**
## **<u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>**

በመደበኛ ሁኔታ በኖቨምበር የመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ይቆያል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ በሰሜን ምሥራቅ፣ በምሥራቅ፣ በመካከለኛውና በደቡብ የሀገሪቱ ደጋማ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ የመጠናከርና በጥቂት ሥፍራዎች ላይም ውርጭ የማስከተል አቅም ይኖረዋል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው እንደሚቆይ የሚጠበቅ ቢሆንም፤ ከዕለት ወደ ዕለት አነስተኛ እርጥበት አዘል አየር ወደ ደቡባዊ አጋማሽ የአገሪቱ ክፍሎች እንደሚገባ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በመሆኑም በዚህ ወቅት ዝናብ በሚጠበቅባቸው በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው ዝናብ አነስተኛ መጠን ያለው እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን፤በጥቂት የሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ ደግሞ አልፎ አልፎ ከሚኖራቸው የደመና ሽፋን በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን የለው ዝናብ የማግኘት ዕድል ይኖራቸዋል።

በዚህም መሠረት በመጪዎቹ አሥር ቀናት በጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ፣ የጋምቤላ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ቦታዎች እንዲሁም በደቡብ ሶማሌ፣ በአርሲና ባሌ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በምሥራቅና በደቡብ ትግራይ እንዲሁም በጥቂት የምስራቅ አማራ አካባቢዎች ላይ አነስተኛ ዝናብ ይኖራል። ቀሪዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ። በሌላ በኩል በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በጥቂት የሀገሪቱ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከሞላ ጎደል እንደሚቀጥል ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 21-30/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት የኖቬምበር ሶስተኛው አስር ቀናት በአብዛኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በተለይም የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብ አመቺ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች ይህንኑ አመቺ ሁኔታ በመጠቀም የደረሱ ሰብሎችን እንዲሰበስቡ ከወዲሁ ይመከራሉ፡፡ በሌላ በኩል የበጋ ወቅት እርጥበት ተተቃሚ በሆኑ የምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ እርጥበቱ በስርጭትም ሆነ በመጠን እንደሚዳከም የተሰጠዉ ትንበያ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮችም ሆኑ ጥምር ግብርና የሚያከናዉኑ የሚጥበቀዉን መጠነኛ እርጥበት ከብክነት በመከላከል ለተፈለገዉ የግብርና ስራ ጥቅም ላይ ማዋል እንዲችሉ አስፈላጊዉን ቅድመ ሁኔታና ዝግጅት እንዲያደረጉ ይመከራሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመጠኑ እንደሚሻሻል የሚጥበቀዉ እርጥበት የአረንገዴ ዕጽዋት ልምላሜንና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦትን ከማሻሻልም አንጻር በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ እንዲሁም በጥቂት የሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃ ያሳያል። በዚህ መሰረት አብዛኛው ገናሌዳዋ፣ ባሮአኮቦ፣ የታችኛው ሪፍትቫለ፣ አብዛኛው ኦሞጊቤ፣ የባሮአኮቦ ደቡባዊው ክፍል፣ የታችኛው ኦጋዴን፣ የላይኛው

ዋቢሸበሌ እና አዋሽ ተፋሰስ ክፍሎች ከመደበኛው በታች የሆነ ዝናብ የሚያገኙ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ተፋሰሶች የሚገኙት መጠነኛ እርጥበት ለግጦሽ ሳርና ለግድቦች በመጠኑም ቢሆን የሚጠቅም ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የታችኛው ተከዜና የላኛው አባይ አነስተኛ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ ይህም የዝናብ መጠን ለግጦሽ ሳር የተወሰነ ጠቀሜታ አለው፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች በደረቃማው የአየር ሁኔታ ላይ ይቆያሉ በመሆኑም ደረቃማው ሁኔታ አካባቢዎችን እንዳይጎዳ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡